# የኢንተርኔት ደህንነት

## መግብያ

ኢንተርኔት መጠቀም የብዙ ሰዎች ዕለታዊ ኑሮ አካል ነው። ብዙ ሰዎች ኦንላይን ስለሚኖራቸው ደህንነት ያስባሉ፣ ነገር ግን የእነሱን መረጃ ማን ማግኘት እንደሚችል ላይገነዘቡ ይችላሉ። ይህ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ኢንተርኔት የሚጠቀሙበት መንገድ፣ ሰንሰቲቭ መረጃ በምን መልኩ እንደሚጠቀሙና አንባቢዎች ስለሚያጋሩት መረጃ ይዘትና የሚያጋሩት ሰው እንዲያስተውሉ ያደርጋል። ስለኦንላይን ደህንነቶ የተለየ ችግር ካጋጠሞት፣ ስለ ሁኔታው ለተጣባቂዎች ማናገር ሊያስፈልጎት ይችላል። እስዎ 24/7 የቨርጂንያ ስቴትዋይድ ሆትላይን በ 1-800-838-8238፣ የፅሁፍ መልእክት 804-793-9999ወይ በቻት vadata.org/chatማግኘት ይችላሉ።

## በኢንተርኔት ላይ፡ የግል ማሰሻና ታሪክ ማፅጃ

በኢንተርኔት ማሰሻዎ ላይ የግል ዊንደው መጠቀም የሚሰጣቸው መጠነ ሰፊ ጥቅሞች አሉ።:: አብዛኞቹ የግል አሳሾች ታሪኮችን አይመዘገብም። ይህም ማለት ሌሎች እርስዎ የሚያዩትን ወይ የሚያስሱትን ነገር ማየት የለባቸውም። ያስታውሱ የሚጠቀሙበት መሳርያ በሌላ መንገድ ክትትል እየተደረገበት ከሆነ የአሰሳ ግለኝነት እንደሚኖር አያረጋግጥም (ለምሳሌ የስለላ መሳርያ፣ ቪድዮ፣ መቅጃ፣ ወዘተ)። ይህ ክፍል በተለያዩ ማሰሻዎች የግል ዊንደው እንዴት እንደሚከፍቱና የተጠቀሙበትን ታሪክ እንዴት እንደሚያጠፉ የሚሸፍን ነው። በሞባይልና ዲስክቶፕ ላይ ተጠቅመው ከጨረሱ በኋላ ሁሉም ማሰሻ ዊንደዎች ማውጣቶን ያረጋግጡ።

### Google Chrome (ጎግል ክሮም)

የግል ወይ ‹‹ኢንኮግኒቶ›› ዊንደው ለመክፈት በኮምፒተሮ ላይ ያለውን አማራጭ ቁልፎችን ተጠቀሙ፡

- ለ Linux፣ ወይ Chrome OS ኮምፒተሮች በተመሳሳይ ግዜ “Ctrl”፣ “Shift” እንዲሁም “N” የሚለውን ይጫኑ።
- ለ Mac OS ኮምፒተሮች በተመሳሳይ ግዜ “⌘” (command/cmd)፣ “Shift”፣ እንዲሁም “N” የሚለውን ይጫኑ።

በተንቀሳቃሽ ስልኮ ‹‹ኢንኮግኒቶ››ትር ለመክፈት፣ ክሮም አይከንኑ ወደ ታች በመጫን “New private tab” የሚለውን ምረጡ፡፡

የዲስክቶፑን የአሰሳ ታሪክ ለማፅዳት ይህን አቋራጭ ቁልፍ ‹‹Ctrl›› እንዲሁም ‹‹H›› ይጠቀሙ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከታሪኮ ለማጥፋት በግል የገቡትን መረጃዎች በመምረጥ ማጥፋት ይችላሉ፡፡ ማጥፋት በፈለጉት ላይ በግራ በኩል ያለውን ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ “Delete” የሚለውን ይጫኑ፡፡

የአሰሳ ታሪክ ከተንቀሳሽ ስልኮ ለማጥፋት ክሮም መተግበርያ (Chrome app) ይክፈቱ፡፡ ዝርዝር አማራጩን በመጫን በመቀጠል ‹‹ History ›› የሚለውን ይምረጡ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለማጥፋት በግል የገቡትን መረጃዎች በመምረጥ ማጥፋት ይችላሉ፡፡

[ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ክሮም የድጋፍ ገፅ (Chrome’s support page) ይጎብኙ፡፡]

## Mozilla Firefox (ሞዚላ ፋየርፎክስ)

የግል ዊንደው ለመክፈት በኮምፒተሮ ላይ ይህን አቋራጭ ቁልፍ መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ለ Linux፣ ወይ Chrome OS ኮምፒተሮች በተመሳሳይ ግዜ “Ctrl”፣ “Shift” እንዲሁም “P” የሚለውን ይጫኑ፡፡
- ለ Mac OS ኮምፒተሮች በተመሳሳይ ግዜ “⌘” (command/cmd)፣ “Shift”፣ እንዲሁም “N” የሚለውን ይጫኑ፡፡

በተንቀሳቃሽ ስልኮ የግል ትር ለመክፈት፣ ፋየርፎክስ አይከንኑ ወደ ታች በመጫን “New private tab” የሚለውን ምረጡ፡፡

ወደ ዲስክቶፕ የሚገባውን የግል መረጃ ለማጥፋት፣ ዝርዝር አማራጩን ይጫኑ፡፡ ‹‹History›› የሚለውን በመምረጥ በመቀጠል  “Manage History” የሚለውን ይምረጡ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ማጥፋት የሚፈልጉትን ድህረ ገፅ ስማቸውን መፃፍ፣ ራይት ክሊክ፣ “Forget about this site” የሚለውን ይምረጡ፡፡

ከተንቀሳቃሽ ስልኮ የሚገባውን የግል መረጃ ለማጥፋት ፋየርፎክ መተግበርያ (Firefox app) በመክፈት ዝርዝር አማራጩን ይጫኑ፡፡ “History” የሚለውን ይምረጡ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለማጥፋት በግል የገቡትን መረጃዎች በመምረጥ ማጥፋት ይችላሉ፡፡

[ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ፋየርፎክስ የድጋፍ ገፅ (Firefox’s support page) ይጎብኙ፡፡]

## Microsoft Edge (ማይክሮሶፍት ኤጅ)

የግል ወይ ‹‹በግል›› ዊንደው ለመክፈት በኮምፒተሮ ላይ እነዚህን አቋራጭ ቁልፎችን መጠቀም ይችላሉ።

- ለ Linux፣ ወይ Chrome OS ኮምፒተሮች በተመሳሳይ ግዜ “Ctrl”፣ “Shift” እንዲሁም “N” የሚለውን ይጫኑ።
- ለ Mac ኮምፒተሮች በተመሳሳይ ግዜ “⌘” (command/cmd)፣ “Shift”፣ እንዲሁም “N” የሚለውን ይጫኑ።

በተንቀሳቃሽ ስልኮ የግል ትር ለመክፈት፣ ኤጅ አይከንኑ ወደ ታች በመጫን “New private tab” የሚለውን ምረጡ።

ወደ ዲስክቶፕ የገባውን ታሪክ ለማጥፋት በቁል አቋራጩን ‹‹Ctrl›› እንዲሁም ‹‹H›› ይጠቀሙ። በታሪክ ዊንደው ከርሰሩን ወደ ብግል የገባ ወደ ሚለው መውሰድ ይችላሉ በእያንዳንዱ ላይ በቀኝ “x” ምልክት ያሳያል። የገባውን ለመሰረዝ “x” የሚለውን ይጫኑ።

ከተንቀሳቃሽ ስልኮ የሚገባውን የግል መረጃ ለማጥፋት ኤጅ መተግበርያ (Edge app) ይክፈቱ። ዝርዝር አማራጩን በመጫን ‹‹ History ›› የሚለውን ይምረጡ። ከዚህ በመቀጠል ለማጥፋት በግል የገቡትን መረጃዎች በመምረጥ ማጥፋት ይችላሉ።

[ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ኤጅ የድጋፍ ገፅ (Edge’s support page) ይጎብኙ።]

## Apple Safari (አፕል ሳፋሪ)

የግል ዊንደው ለመክፈት በኮምፒተሮ ላይ ይህን አቋራጭ ቁልፍ መጠቀም ይችላሉ።

- ለ Mac ኮምፒተሮች በተመሳሳይ ግዜ “⌘” (command/cmd)፣ “Shift”፣ እንዲሁም “N” የሚለውን ይጫኑ።

በተንቀሳቃሽ ስልኮ የግል ትር ለመክፈት፣ ሳፋሪ (Safari) አይከንኑ ወደ ታች በመጫን “New private tab” የሚለውን ምረጡ።

የአሰሳ ታሪኮን ከታሪክ ለማጥፋትና ሙሉ የአሰሳ ተሪኮን ለማየት “⌘” (command/cmd) እንዲሁም “Y” የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ። ከዚህ በመቀጠል “Ctrl” የሚለውን መንካትና በግል ወደ አሰሳ ታሪክ የገባውን መምረጥና ከታች ካለው ዝርዝር ‹‹ Delete›› አማራጭ የሚለውን ይምረጡ።

በግል የሚገቡትን ነገሮች ከተንቀሳቃሽ ስልኮ ማጥፋት ከፈለጉ፣ ሳፋሪ መተግበርያ (Safari app) በመክፈት ቡክማርክ አይከን ይንኩ። ከዚህ ቀጥሎ ታሪክ የሚለውን መለያ ይምረጡ። ማጥፋት በሚፈልጉት ማንኛው የሚገባ ነገር ወደ ግራ ያንሸራቱ።

[ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ኤጅ የድጋፍ ገፅ (Safari’s support page) ይጎብኙ።]()

## የሚጠቀሙበት መሳርያ: ማን መዳረሻ አለው?

ስልኮን፣ ኮምፒተርና ሌሎች ቴክኖሎጅያዊ መሳርያ የማግኘት ዕድል ያለውን ሰው ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሆነ ሰው ይህን ማግኘት የሚችልበት የተለያዩ መንገዶች አሉ። የመግብያ መንገድ (እንደ ሚስጥር ቁጥር) ለሌላ ሰው አጋርተው ሊሆን ይችላል። የሆነ ሰው የእርስዎን ፈቃድ ሳያገኝ የመግብያ መንገድ አግኝቶ ሊሆን ይችላል። የሆነ ሰው በሚጠቀሙበት መሳርያ ላይ የስለላ መሳርያ ገጥሞ ሊሆን ይችላል። ሰንሰቲቭ የሆነ ጉዳይ ከመጠቀሞ በፊት የሚጠቀሙበትን መሳርያ የማግኘት እድል ያለው ሰው ካለ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርቦታል።

የሆነ ሰው የሚጠቀሙበትን መሰርያ እየተከታተለ ነው ብለው ካሰቡ፤ ሰንሰቲቭ ወይ ሚስጥራዊ የሆኑ ጉዳዮችን በሌላ መሳርያ መጠቀም ሊኖርቦት ይችላል። ግምት ውስጥ የሚያስገቧቸው ብዙ አማራጮች አሉ። በቤተ መፅሀፍት እንደሚገኙት ለህዝቡ በነፃ የሚቀርቡትን ኮምፒተሮች መጠቀም ይችላሉ። እንዲሁም እንደ ጓደኛና ቤተሰብ የመሳሰሉትን ሰዎች መሳርያ ለመጠቀም መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎ ብቻ የሚያውቁት ሌላ መሳርያ መግዛት ይችላሉ። ሰንሰቲቭ የሆነ ጉዳይ ወደ ሌላ መሳርያ ከወሰዱ፤ መጀመርያ ሲጠቀሙበት በነበረው መሳርያ ከዚህ ቀደም በሚጠቀሙበት መንገድ መጠቀም መቀጠል አለቦት። በሚጠቀሙት መሳርያ ላይ በልምድ መጠነ ሰፊ ለውጥ ካደረጉ እንደሚከታተሎት የሚያውቁት ሰው እንዲያውቅ ሊያደርገው ይችላል። ይህም ሰዎችን ሊያበሳጭ ወይ ግጭት ሊያባብስ ይችላል።

## ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ኦንላይን የሚጠቀሙበት መንገድ፡ ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት ኮኔክሽን

ደህንነቱ የተጠበቀ ኢንተርኔት ኮኔክሽን እርሶንና መረጃዎን ከውጭ ጥቃት ይከላከልሎታል። በእርስዎ ቁጥጥር ስር ያለውን ኢንተርኔት እየተጠቀሙ ከሆነ፤ ማለትም የግል ራውተር ወይ ሆትስፖት እየተጠቀሙ ከሆነ ደህንነቶን ለመጠበቅ የሚወስዷቸው እርምጃዎች አሉ። አንደኛው ጠንካራ ሚስጥር ቁጥር እንዲኖረው ማድረግና ለብዙ ሰው አለማጋራት ነው።

በተለይም የኢንተርኔት ኮኔክሽኖን እንዲጠቀሙ የማይፈልጓቸው ሰዎች ካሉ በየጊዜው የሚስጥር ቁጥሮን መቀየር ጥሩ ነው። ክፍት ኔትዎርክ ማለት በስፋት የሚታወቅ ሚስጥር ቁጥር ያላቸው ወይ ሚስጥር ቁጥር የሌላቸው ናቸው። ክፍት ኔትዎርክ በሚጠቀሙበት ወቅት አማራጮችን ይጠቀሙ።

በURL ‹‹ HTTPS›› የሚል ፅሁፍ ያላቸው ድህረ ገፆች ከሌላቸው ይልቅ ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው። ኮምፒተር በሚጠቀሙበት ወቅት ድህረ-ገፁ ‹‹ HTTPS›› የማይጠቀም ከሆነ ገፁ ደህንነቱ ያልተጠበቀ እንደሆነ ያሳውቆታል። ስልክ እየተጠቀሙ ከሆነ በገፁ URL በመንካት ‹‹ HTTP›› ሳይሆን ‹‹ HTTPS›› የሚል መኖሩን ያረጋግጡ። ያስታውሱ ‹‹ S›› የሚለው ፊደል ‹‹ደህንነት›› የሚለውን ነገር ያመላክታል። ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ ላይ ሲሆኑ ስልኮን ወደ ሆትስፖት መቀየር ከቻሉ፣ ደህነቱ የተጠበቀ ኔትዎርክ እንዲጠቀሙ ያስችሎታል።

## ማጠቃለያ

በዚህ ውስጥ ያሉት ቲፖች ቴክኖሎጂን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የሚጠቀሙበትን መንገድ ያሳያል። የዚህ ዓላማ በተቻለው አቅም ኢንተርኔት ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ መጠቀም እንዲችሉ በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ እንዲወስኑ ለማስቻል ነው። ችግር ወይ ጥያቄ ካሎት፣ ስለሁኔታው ለመነነጋገር ወደ ቨርጂንያ ስቴት ዋይድ ሆትላይን መደወል ይችላሉ። ተጣባቂዎኡ 24/7 በ1-800-838-8238 በመደወል፣ በ 804-793-9999 ፅሁፍ መልእክት ወይ በ vadata.org/chat ማናገር ይችላሉ። ሁሉም አገልግሎቶች ነፃና ሚስጥራዊ ሲሆኑ የቋንቋ ትርጉም አገልግሎት ተዘጋጅቷል።